# 🌹ድርሳነ 🌹ቄርሎስ 🌹ወጸላድዮስ 🌹ወተረፈ ቄርሎስ 🌹ተከታታይ 🌹ትምህርት



አዘጋጅ፡- መ/ር በትረ ማርያም አበባው (የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር & BSC Civil Engineering)

## መግቢያ

ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በኤፌሶን ጉባዔ ለ200ው ሊቃውንት አፈ ጉባዔ የነበረና ንስጥሮስን የረታ ታላቅ ሊቅ ነው፡፡ ይህ ቄርሎስ ትምህርት በጀመረ በአምስት ዓመቱ የብሉይ ኪዳንንና የሐዲስ ኪዳንን ትርጓሜ ተምሮ ያጠናቀቀ ቅዱስ ሊቅ ነው፡፡ ሲያስተምርም ከአንደበቱ ርቱዕነት ከጣዕመ ቃሉ ፍጹምነት ከትምህርተ ጥቅሱ ምሥጢርና ከምክሩ ከተግሣፁ የተነሣ የሚሰሙት ሁሉ ትምህርቱን አቋርጦ ይተውብን ይሆን ምነው ቢጨምርበት እያሉ ልቡናቸውን በተመሥጦ ሰቅለው ሕሊናቸውን አቅንተው ይሰሙት ነበር እንጂ አይሰለቹትም ነበር፡፡ ስመ ሥርጋዌው (የክብር ስሙ) መምህረ ዓለም ይባላል፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ ይህንን መጽሐፍ የጻፈው ከጉባዔ ኤፌሶን ጀምሮ ባለው ጊዜ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ወልደ አብ ወልደ ማርያም መሆኑን ወልደ ማርያም ወልደ አብ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ በሥጋ መሆኗን ይገልጻል፡፡ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህ መጽሐፍ ውስጥ ለብዙ ከሓድያን ምላሽ ይሰጣል፡፡

፩፦ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው ለሚል ለማኒ

፪፦ ቃል ወደ ሥጋ ተለወጠ ለሚሉ ለሐራ ጥቃ

፫፦ የቃል መነሻ ከማርያም ወዲህ ነው ለሚሉ

፬፦ የቃል አካል አልነበረውም ለሚሉ

፭፦ ለሥጋ በነፍስ ምትክ መለኮት ሆነው ለሚሉ

፮፦ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ለሚሉ

እና ለመሳሰሉት ሁሉ ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡ የቃል መነሻ ከማርያም ወዲህ ነው የሚሉ እነ ፎጢኖስ ናቸው፡፡ ክርስቶስ ነፍስ የለውም በነፍሱ ምትክ መለኮቱ ሆነው የሚሉ እነ አቡሊናርዮስ ናቸው፡፡ ክርስቶስን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ የሚል ንስጥሮስ ነው፡፡ ቃል ዝርው ነው አካል አልነበረውም የሚሉ እነ መርቅያን ናቸው፡፡ ድርሳነ ቄርሎስን መማር ለሚፈልጉ ሼር አድርጉላቸው፡፡ ድርሳነ ቄርሎስ በደንብ ግልጽ እንዲሆንላችሁ በተከታታይነት የተማማርነውን ሃይማኖተ አበው በPDF በቴሌግራም ቻናሌ ያገኙታል፡፡

## ❁ድርሳነ ❁ቄርሎስ ❁መቅድም

ቄርሎስ ማለት አንበሳ ኃያል ኀሩይ (የተመረጠ፣ ምርጥ) ማለት ነው፡፡ አንበሳ መባሉ መ*ፍቃ*ንን እንደ አንበሳ በኃይለ ቃል ይሰብራቸዋልና ነው፡፡ የቅዱስ ቄርሎስን እናት ያሳደገቻት ኢትዮጵያዊት አገልጋይ ናት፡፡ ይህች ኢትዮጲያዊት መጀመሪያ ጣዖት አምላኪ ነበረች፡፡ በኋላ ቅዱስ አትናቴዎስን አጥምቀኝ ብላው ተጠምቃለች፡፡ ቴዎፍሎስ ሲሞት በእርሱ ምትክ ቅዱስ

ቄርሎስ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኗል። ቅዱስ ቄርሎስ አፈጉባዔ ሆኖ የረታው መና*ቅ ንስጥሮስ ነው።

ንስጥሮስ የዲያድርስ የአጎቱ ልጅ ነው። ዲያድርስ የጳውሎስ ሳምሳጢ ደቀ መዝሙር ነው። ዲያድርስ ክሕደቱን ከጳውሎስ ሳምሳጢ ተማረ። ንስጥሮስ ደግሞ ክሕደቱን ከዲያድርስ ተማረ። ጳውሎስ ሳምሳጢ ግን ክሕደቱን ከዲያብሎስ ተምሮታል። ንስጥሮስ ከዲያድርስ የተማረውን ክሕደት ፐትርክና ሲሾም ገለጠው። አንዱን ክርስቶስን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ነው አለ። ቅዱስ ቄርሎስ ይህንን በሰማ ጊዜ አከራክረኝ ብሎ ወደ ንጉሡ ቴዎዶስዮስ ላከበት።

ንጉሡም በኤፌሶን ጉባዔ እንዲሆን አዘዘ። 200 ሊቃውንት በአንድነት ሆነው ንስጥሮስን አውግዘው ለይተውታል። ቅዱስ ቄርሎስ በመዓርጉ ከሐዋርያት ከነቢያት የደረሰ ነበር። ንስጥሮስን ክሕደትን የካደች ምላስህ አትታዘዝህ ቢለው ምላሱ ተጎሎጉሎ ወጥቶ እንደውሻ ጓጉሮ ሞቷል። ቅዱሳን ምንም ባይከራከሩ ከጉባዔ አይለዩም። ቄርሎስ ምሥጢረ ተዋሕዶን በነበልባልና በሐመልማል፣ በእሳትና በብረት፣ በነፍስና በሥጋ ተዋሕዶ እየመሰለ ያስተምር ነበር።

## ♥ምዕራፍ ፩

በዚህ መጽሐፍ እስከ ምጽአት የሚነሱ ሊቃውንት መ*ና*ቃንን ሲረቱበት ይኖራሉ። ትክክለኛዋ ሃይማኖት ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ የምትል ናት። ሰውን ጻድቅ ቢሉት ሐሰት፣ ንጹሕ ቢሉት ኃጢአት፣ ባዕል ቢሉት ንዴት ይስማማዋል። እግዚአብሔር ግን ጻድቅ ዘአልቦ ሐሰት፣ ንጹሕ ዘአልቦ ኃጢአት፣ ባዕል ዘአልቦ ንዴት ነው።

## ♥ምዕራፍ ፪

ናባል ዳዊት መጣ ቢሉት ደንግጦ እንደሞተ ሁሉ ነቢያት ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል ብለው ሲያስተምሩ አጋንንት ይወጡ ነበረ። ዳዊት ኢዮአብን አቢሳን እየሰደደ ድል ያደርግ እንደነበረ ጌታም ነቢያትን እየሰደደ አጋንንትን ያስወጣ ነበረ።

## ♥ምዕራፍ ፫

በአራቱ መዓዝን ምሉዕ ለሆነ ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲገባ ለቅዱሳንም የአክብሮት ስግደት መስገድ ይገባል። የሀብተ መንግሥት አስገኘ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ በእውነተኛ ሃይማኖት ጸንተው ለሚወዱት ሰዎች ክህነትን መንግሥትን ፈጽሞ ይሰጣል።

## ♥ምዕራፍ ፬

ነገሥታት አምልኮተ እግዚአብሔርን ቢይዙ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጣቸው የጸጋ ክብር አለ። ከእግዚአብሔር ትእዛዝ መውጣት አይገባም። አምላክ ሥነ ፍጥረትን የፈጠረ ለሰው ነው።

## ❤ምዕራፍ ፭

ሰናክሬም በትዕቢት ሆኖ እግዚአብሔርን ተሳደበ። ንጉሡ ሕዝቅያስ ጌታ ሲሰደብ ሰምቶ ልብሱን ቀደደ አሰለበ። ልብስን መቅደድ የኀዘን ምልክት ነው። (እግዚአብሔር ሲሰደብ፣ ቤተክርስቲያን ስትሰደብ ማዘን ይገባል)።

## ❤ምዕራፍ ፮

ሕዝቅያስ ጌታ ሲሰደብ በማዘኑ ጠላትን የማሸነፍ ሀብትን ከእግዚአብሔር ዘንድ አገኘ። ብዙ ሠራዊት የነበረው ሰናክሬምንም አሸነፈው። እግዚአብሔርን የማምለክ ፍሬው ይህ ነው። እኛ ምክንያት ሆነን እግዚአብሔርን ማሰደብ አይገባንም።

## ❤ምዕራፍ ፯

ንጉሥ አኖሬዎስ ንጹሕ ድንግል ነው። ዐቢይ ጾምን ገዳመ አስቄጥስ እየሄደ ይጾም ነበር። ሐሰት የሌለባት አንድ አካል አንድ ባሕርይ የምትል ሃይማኖትን ለነፍሳችሁ ጌጥ አድርጓት። ሃይማኖት የልቡና መደገፊያ፣ የሰውነት ተድላ ደስታ፣ የራስ ዘውድ ናት።

## ❤ምዕራፍ ፰

አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሚሆን የክርስቶስን የሰውነቱን ነገር የአምላክነቱን ነገር ጥቂት እናገራለሁ። ሳልሰለች ወድጄ ሳልታክት ተግቼ እናገራለሁ። ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ማለት ያልቀና፣ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ማለት የቀና ትምህርት ነው። ወጥመድ ይዛ ለዳኞች እንድታቀይ ክሕደትም ለፍዳ ታቆያለች።

## ❤ምዕራፍ ፱

ነቢያት ሐዋርያት ካስተማሩት ትምህርት ወጥተው ክፉ ጥፉ በምትሆን በደዌ ክሕደት የተያዙ አሉ። ክርስቶስ ከአብ ወጥቼ መጣሁ ያለውን ይዘው ቃል የተዋሐደው ሥጋ በቅድምና ነበረ የሚሉ ከሓድያን ነበሩ። እነዚህም እነ አፍትኪስ ናቸው። ቃል ለሰው ጸጋን ክብርን ለመስጠት ሰው ሆነ። ሥጋ ተለውጦ መለኮት ሆነ ማለት ክሕደት ነው።

## ❤ ምዕራፍ ፲

እነ ንስጥሮስ ተዋሕዶን ክደው ከድንግል ማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ነው ከአብ የተወለደው የባሕርይ አምላክ ነው ብለው ይክዳሉ። ነገር ግን አምላክ ሰው ካልሆነ ክርስቶስ አይባልም። ክርስቶስ ካልተባለ ክርስቲያን መባል የለም። መጻሕፍት በተናገሩት መምህራን ባስተማሩት መጽናት ይገባል።

## ❤ምዕራፍ ፲፩

የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው የሚሉ ከሓድያን ነበሩ። ይህም ማለት የሚዳሰስ ይመስላል

እንጂ አይዳሰስም የሚሉ ከሓድያን ናቸው። ድንግል ማርያም ጌታን በወለደችው ጊዜ አውራ ጣቱን አሰረችው። ይህም ምትሐት አለመሆኑን ያስረዳናል። ምትሐት የሚዳሰስ የሚታሰር ነገር የለውምና። ክርስቶስ መከራን መቀበሉ፣ መራቡ፣ መጠማቱ፣ መሞቱ ምትሐት አለመሆኑን ያስረዳል።

## ❤ምዕራፍ ፲፪

ጌታ ጀርባውን መገረፉ፣ ፊቱን መመታቱ፣ እጁን እግሩን በችንካር መቸንከሩ፣ በመስቀል ሲሰቀል ጎኑን በጦር መወጋቱ፣ ሲወጋ ከጎኑ ክቡር ደም ከውሃ ጋር መፍሰሱ ምትሐት አለመሆኑን ያስረዳል። ምትሐት ደም የለውም፣ ምትሐት መከራ አይቀበልም፣ ምትሐት አይመታም። ምትሐት መስሎ የሚታይ ሐሰተኛ ነው እንጂ እውነተኛ አይደለም።

## ❤ምዕራፍ ፲፫

ቃል ሥጋ ሆነ የሚለውን ይዘው ቃል ሥጋ ወደ መሆን ተለወጠ ብለው የሚናገሩ ከሓድያን አሉ። ነገር ግን ቃል ሥጋን ተዋሐደ እንጂ ወደሥጋነት አልተለወጠም። ተለወጠ ማለት ተዋሕዶን መካድ ነው። በቃል መለወጥ የለበትም። በጽኑዕ ባሕርይ ያለ መለኮት ከባሕርዩ አይናወጥምና። መለወጥ የሚስማማ ለፍጡራን ነው እንጂ ለፈጣሪ አይደለም። መለኮት መቸም መች ፈጽሞ አይለወጥም።

## ❤ምዕራፍ ፲፬

የመለኮት ባሕርይ እንደማይለወጥ ቅዱስ ዳዊት አንተ ግን ያው አንተ ነህ ብሎ ተናግሯል (መዝ.፻፩፣፳፯)። በጊዜ ተዋሕዶ መለኮት ወደሰውነት እንዳልተለወጠ ሁሉ ሰውነትም ወደመለኮትነት አልተለወጠም። አማኑኤል ከእመቤታችን እንደተወለደ በእውነት እናምናለን።

## ❤ምዕራፍ ፲፭

ሥጋ ከእመቤታችን ሲገኝ ቃል ከአብ ተገኘ የሚሉ ከሓድያን ነበሩ። የወልድ አካል ከዓለም በፊት እንደነበረ አያምኑም። ነገር ግን ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበር ብሎ ክሕደታቸውን ያፈራርስባቸዋል (ዮሐ.፰÷፰)። ጌታም አብርሃም ሳይወለድ ነበርኩ ስለሚልባቸው በዚህ ይሸነፋሉ።

## ❤ምዕራፍ ፲፮

ቃለ እግዚአብሔር እንደእኛ እንደሰዎች ቃል ዝርው ነው አካል የለውም የሚሉ ከሓድያንም ተነስተው ነበር። አብን የካደ ወልድን የካደ ነው። ወልድን አካላዊ ተወላዲ ብሎ ያላመነ አብን አካላዊ ወላዲ ብሎ አያምንም። አብ የሌለበት ጊዜ እንደሌለ ወልድ የሌለበት ጊዜ የለም።

## ❤ምዕራፍ ፲፯

በእውነትስ አብ በወልድ ህልው ነው። ወልድን የለም ማለት አብንም የለም ማለት ነው። ቃለ

እግዚአብሔር በአካላዊነት የለም ማለት ሐሰት ነው።

## ❦ምዕራፍ ፲፰

*ቃል* በተዋሐደው *ሥጋ* ነባቢት ነፍስ የለችም በነፍስ በልቡና ስፍራ መለኮት ገባ የሚሉ ከሓድያን ነበሩ። እኛስ *ቃል* ከድንግል ማርያም *ሥጋን* ነፍስን ነስቶ እንደተዋሐደ እናምናለን። ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ እንደሆነ እናምናለን። በተዋሕዶ በተዓቅቦ አንድ እግዚእ፣ አንድ ወልድ እንደሆነ እናምናለን። መለየት ሳይኖርበት በተዋሕዶው ጸንቶ ይኖራል።

## ❦ምዕራፍ ፲፱

*ቃል* ፍጹም *ሥጋን* ፍጹም ነፍስን ተዋሕዶ ሰው ሆነ። አብን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው አንድ ወልድ የሚሆን *ቃል* እኛን ለማዳን ሰው ሆነ።

## ❦ምዕራፍ ፳

ክርስቶስ *ሥጋችንን* በመወሐዱ ለእኛ *ሥጋ* ልጅነትን ትንሣኤን ሰጠን። ነፍሳችንን በመዋሐዱ ከኃጢአት አዳነን። *ሥጋ* ሁሉን የሚያድን የ*ቃል* ገንዘብ ሆኖ ከሞት ከሙስና ድኖ ይኖር ዘንድ *ቃል* *ሥጋን* ተዋሐደ። ነፍስም ኃጢአት የሌለባት የ*ቃል* ገንዘብ ሆና ከኃጢአት ድና ትኖር ዘንድ *ቃል* ነፍስን ተዋሐደ።

## ❦ምዕራፍ ፳፩

ኵለንታ *ቃል* ኵለንታ ትስብእትን እንደተዋሐደ እናምናለን። በ*ሥጋ* ክሶ *ሥጋችንን* ያድን ዘንድ በነፍስ ክሶ ነፍሳችንን ያድን ዘንድ *ቃል* *ሥጋን* ነፍስን ተዋሐደ። መለኮት በምልዐት የሚኖር ነው። በተዋሕዶ *ሥጋ* የማይለወጥ የ*ቃል* ገንዘብ ሆኗል። ክርስቶስ በአጸደ *ሥጋ* ላሉ በአካለ *ሥጋ* ታይቶ እንዳስተማረ በአጸደ ነፍስ ላሉትም በተዋሕዶ ገንዘብ ባደረጋት በአካለ ነፍስ ታይቶ አስተማረ። የተዋሕዶ ም*ሥ*ጢር ረቂቅ ነው አይመረመርም። መርምሮ ማወቅ የማይቻለውን መርምሬ አውቃለሁ ማለት አእምሮ ማጣት ነው።

## ❦ምዕራፍ ፳፪

ሃይማኖታችን ነገር በማሳመር አይደለም። በሰው ልባምነት የተመሠረተም አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በገለጸው ትምህርት ነው እንጂ። የአብ አካላዊ *ቃል* ለዘለዓለም ባለመለወጥ ጸንቶ ይኖራል። ሰውም ከሆነ በኋላ ባለመለወጥ ጸንቶ ይኖራል። በከመ ሀሎ በመለኮቱ ፍጹም። ቅድመ ተዋሕዶ በመለኮቱ ፍጹም እንደነበረ። ከማሁ በትስብእቱ ፍጹም። ሰውም ከሆነ በኋላ በሰውነቱ ፍጹም ነው። ሰው የሆነ አምላክ ነው። አምላክ የሆነ ሰው ነው።

## ❦ምዕራፍ ፳፫

ከተዋሕዶ በኋላ *ቃልን* ከ*ሥጋ* መለየት ክሕደት ነው። ትስብእትን ከመለኮት መለኮትን ከትስብእት ለይቶ የሚናገር አማኑኤልን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ያሰኘዋል። እኛስ ከሁለት

ተገኝቶ አንድ እንደሆነ እናውቃለን እንጂ ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ነው አንልም።

## ምዕራፍ ፳፬

ነቢዩ ዳዊት ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ ካለው ወአነ ዮም ወለድኩከ ያለው ደኃራዊ ልደቱን ያስረዳል። ከአብ ጋር በቅድምና የነበረ ወልድ ባሕርዩን ሳይለቅ ሰው ሆኗል። የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ በነፍስና በሥጋ አምሳል እንደሆነ እናውቃለን። ቃል ሰው ሳይሆንም አንድ ነው። ሰውም ከሆነ በኋላ አንድ ነው።

## ምዕራፍ ፳፭

ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ ማለት ክሕደት ነው። ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው።

## ምዕራፍ ፳፮

መላእክት የክርስቶስ ተገዢዎች ናቸው። እግዚአ ስብሐት ክርስቶስ ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ቃልን ከሰውነት ሥራ ለይተን ልናወጣው አይገባም። ሥጋንም ከአምላክነት ክብር ልናወጣው ፈጽሞ አይገባም። ከተዋሕዶ በኋላ መለኮቱን ከትስብእቱ ትስብእቱን ከመለኮቱ ለይቶ የሚናገር ሰነፍ አእምሮውን ያጣ ነው።

## ምዕራፍ ፳፯

ቃልን ከትስብእት ለይተን ትስብእቱንም ከመለኮት ለይተን ክርስቶስ ልንለው አይገባንም። ሞተ በሥጋ ባልን ጊዜ በመለኮቱ ሕያው ነው ማለታችን ነው።

## ምዕራፍ ፳፰

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ። ቃል ሰው ሆነ እንደተባለ ሥጋ አምላክ ሆነ ተባለ። ቃል በጌትነቱ የጸና ሲሆን ሥጋን ስለተዋሐደ በኵረ ምእመናን ተባለ።

## ምዕራፍ ፳፱

ሐዋርያት ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ አውቀው ሰገዱለት። አንዱ ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ ይባላል። ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

## ምዕራፍ ፴

ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ በእውነት የክብር ባለቤት ነው። ትክክለኛዋ ሃይማኖት አንዲት ናት። ይህችውም በክርስቶስ የምናምናት ሃይማኖት ናት። ለሥላሴ የምንሰግዳት ስግደትም አንዲት ናት። ክርስቶስ አብን ያየ እኔን አየ ብሏል። በዚህ ጊዜ የአብ መታየት በግዘፍ አይደለም። በሥልጣን በክብር በሥራው (በግብሩ) መታየቱን ያስታውቃል እንጂ። አካላዊ ቃል ስለእኛ ሰው ሆነ።

## 🌹ምዕራፍ ፴፩

የክርስቶስ ረቂቅ መለኮቱ እንደማትታይ የታወቀ ነው፡፡ ነገር ግን ረቂቅ መለኮቱ ገንዘብ ባደረገው በሥጋ ታየ፡፡ ሥጋ የቃል ገንዘብ ሆኗልና፡፡ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተውም በሦስተኛው ቀን የተነሣውም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ከአብ የተገኘ ቃል የባሕርይ አምላክ እንደሆነ የሚታመን ከተዋሐደው ሥጋ ተለይቶ አይደለም፡፡

## 🌹ምዕራፍ ፴፪

ክርስቶስ ገንዘቡ የሚሆን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን በረቂቅ ሥልጣኑ ከባሕርዩ ይሰጣል፡፡ በልጅነት የከበርን ሰው በሆነ አምላክ ነው እንጂ በዕሩቅ ብእሲ አይደለም፡፡ ንሬኢ ከመ ያብዕላ ለሥጋሁ ስብሐተ መለኮቱ፡፡ በጌትነቱ ክብር ሥጋን እንዳከበራት እናውቃለን፡፡ በአምላክነት ክብር ሲል ነው፡፡

## 🌹ምዕራፍ ፴፫

የክርስቶስ ሥጋው ከድንግል ማርያም የተገኘ እንጂ ከሰማይ የወረደ አይደለም፡፡ ቃልም በባሕርዩ ምግብ አይደለም፡፡ ከሰማይ የወረደው ቃል ሥጋን ገንዘብ አድርጎ በሥጋ የሕይወት ምግብ ሆነ፡፡ ሥጋም ቃልን ገንዘብ በማድረጉ በቃል ከሰማይ የወረደ ተባለ፡፡ አማኑኤል ከእመቤታችን እንደተወለደ እናምናለን፡፡ ነነብር ምስለ ቅዱሳት መጻሕፍት፡፡ ከመጻሕፍት ጋራ አንድ ነን፡፡ ቃል ጌትነቱን ሳይለቅ ሰው ሆነ፡፡ አምላክ ወሰብእ ነውና የሰውነትም የአምላክነትም ሥራ በአንድ በክርስቶስ ይሠራል፡፡

## 🌹ምዕራፍ ፴፬

አማኑኤል ከድንግል ማርያም ያለቱሳሔ ያለውላጤ እንደተወለደ እናምናለን፡፡ አካላዊ ቃልን ያለ ትስብእት፣ ትስብእትንም ያለ መለኮት ሳናዋሕድ ክርስቶስ ማለት አይገባም፡፡

## 🌹ምዕራፍ ፴፭

እስመ ክርስቶስ ብሂል አሐዱ እምክልኤቱ ብሂል፡፡ ክርስቶስ ማለት በተዋሕዶ ከበረ ማለት ነው፡፡ ጥንቱን በባሕርዩ ሥጋ የሌለው፣ በባሕርይው የማይታይ ቃል በሥጋ ታይቷልና፡፡

## 🌹ምዕራፍ ፴፮

ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ መሞቱና በሦስተኛ ቀን መነሣቱ ለእኛ ሕይወት ሆነን፡፡ ቃል በባሕርይው የማይሞት ሕያው ሕይወት ነው፡፡ መለኮት በሥጋ ሞተ እንላለን፡፡ ክርስቶስ ሞቶ በመነሣቱ አምላክ ወሰብእ መሆኑን ያስረዳል፡፡

## 🌹ምዕራፍ ፴፯

የመጻሕፍትን ነገር ይዘን፣ የአባቶችን ሃይማኖት ወደን ጸንተን እንኖራለን፡፡ ከማትለይ

ከማትመረመር ተዋሕዶ በኋላ ቃልን ከትስብእት አንለየውም። አንድ ክርስቶስ ከሁለት የተገኘ እንደሆነ እናምናለን። አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብለው የሚያምኑ ሰዎች ዋጋቸው ብዙ ነው። በሥጋ ከዳዊት ወገን የተወለደ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት የባሕርይ አምላክ ነው።

### ምዕራፍ ፴፰

በጎ ሃይማኖት በጎ ምግባር ካለች ዘንድ የተረዳ ተስፋ አለ። መንግሥተ ሰማያት ይገኛል። አማኑኤል የባሕርይ አምላክ እንደሆነና ድንግል ማርያምም ወላዲተ አምላክ እንደሆነች እናምናለን።

### ምዕራፍ ፴፱

ክርስቶስ የሁላችን ፈጣሪ ነው። አካላዊ ቃል በኃጢአት የተሰነካከለ አዳምን ያድን ዘንድ ሰው ሆነ።

### ምዕራፍ ፵

ቃል ከድንግል የነሣውን ሥጋ ገንዘብ አድርጓል። ሥጋ በተዋሕዶ የእርሱ ገንዘብ ሆኗልና በሥጋ እንደተወለደ እንናገራለን። ድንግል ማርያም ሰው የሆነ አምላክን በሥጋ ወለደች። ሥግው ቃልን ወለደች እንጂ ዕሩቅ ብእሲን አልወለደችም። ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ዕሩቅ ብእሲ ቢሆን ኖሮስ መላእክት ባልሰገዱለትም ነበር። ክርስቶስ ስለእኛ በሥጋ ሞተ። የክርስቶስ ሞት ሁሉን አዳነ።

### ምዕራፍ ፵፩

በሥጋ የታመመና የሞተ ቃል ከአብ ባሕርይ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው። አንድ ክርስቶስን ሁለት የሚሉ ካዱ።

### ምዕራፍ ፵፪

ኢየሱስን ከአብ የተገኘ ቃል ብንለው ወዲህም ሰው እንደሆነ እንናገራለን።

### ምዕራፍ ፵፫

ከአብ የተወለደው ከእመቤታችን ከተወለደው ልዩ ነው የሚል የተወገዘ ነው።

### ምዕራፍ ፵፬

በመለኮቱ የማይያዝ ክርስቶስ በሥጋ መያዝ ተያዘ። በመለኮቱ ድካም የሌለበት እርሱ በሥጋ መድከም ደከመ። በመለኮቱ አደገ የማይባል እርሱ በሥጋ አደገ ተባለ።

### ምዕራፍ ፵፭

ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ ሳለ የሰውነትን ሥራ ሠራ። ቃል ከጌትነት

ሳይለይ ሰው ሆነ። ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው። በሰውነቱ ያይደለ በመለኮቱ ታመመ የሚል የተወገዘ ይሁን።

## 💐ምዕራፍ ፵፮

ክርስቶስ መለኮቴ አምላክ ነው ነፍስና ሥጋዬ አምላክ አይደለም ብሎ አላስተማረም። ይህ ምንታዌ ነውና። ክርስቶስን የአብ የባሕርይ ልጅ እንለዋለን እንጂ የጸጋ ልጅ አንለውም። ሥጋ የባሕርይ ክብርን አገኘ እንላለን እንጂ የጸጋ ክብርን አገኘ አንልም።

## 💐ምዕራፍ ፵፯

አንዱ ክርስቶስ የሰውነትንም የአምላክነትንም ሥራ ይሠራል። ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ክርስቶስ እንደተባለ እንናገራለን። ከተዋሕዶ በፊት የባሕርይ ክብር ያልነበረው ሥጋ አንድ አካል አንድ ባሕርይ በመሆን ከቃል ጋር ሲዋሐድ የባሕርይ ክብርን ገንዘብ አደረገ።

## 💐ምዕራፍ ፵፰

የክርስቶስ ሕማም ሞት የዓለም መድኃኒት ሆነ። ክርስቶስ ሕይወት በመሆኑ ሞትን ድል አደረገ። ሥግው ቃል የባሕርይ አምላክ ነው።

## 💐ምዕራፍ ፵፱

የአብ ገንዘብ የሚሆን (በከዊነ እስትንፋስነቱ) መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስም ገንዘብ ነው። መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ አካላዊ ሕይወቱ ነውና።

## ✿ምዕራፍ ፶

ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው። ክርስቶስ በገዛ ሥልጣኑ በገዛ ገንዘቡ በመንፈስ ቅዱስ ያድናል። በሐዋርያት አድሮም ተአምራት ያደርጋል። ምእመናን የእግዚአብሔር ተገዢዎች ናቸው።

## ✿ምዕራፍ ፶፩

ክርስቶስ ከእኛ እንደ አንዱ ያለ ዕሩቅ ብእሲ አይደለም። ቅድመ ዓለም የነበረ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ነው እንጂ።

## ✿ምዕራፍ ፶፪

መለኮት በአንድ ህላዌ ጸንቶ ይኖራል። ክርስቶስ ሁሉን እንዳስገኘ እንናገራለን። ቃል ቅድመ ዓለም ከአብ ተወለደ። ዳግመኛ በሥጋ ከድንግል ማርያም ተወለደ። ከተዋሕዶ በኋላ መለኮቱ ከትስብእቱ ትስብእቱ ከመለኮቱ ልዩ ነው የሚል ከአይሁድ ጋር ይቆጠራል።

## ✿ምዕራፍ ፶፫

ለምእመናን ሐዋርያትን፣ መምህራንን የሾመ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በክርስቶስ ሥራ አብን አወቅነው። የሐዋርያት ትጋታቸው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ ነው። ክርስቶስን በማገልገል ልንኖር ይገባል። በደሙ ሁላችንን አድኖናልና።

## ✿ምዕራፍ ፶፬

ራሳችንን በሃይማኖት በምግባር እናጸናለን። የእግዚአብሔር ማኅደር እኛ ምእመናን ነን። ወልድ ሰው መሆንን ሳይንቅ ሳይጠላ ሰው ሆነ። አሪት ወደ ክርስቶስ መራችን። እግዚአብሔርን ለማወቅ መሪ ሆነችን። በእግዚአብሔር (በሥግው ቃል) እንመካለን እንጂ በዕሩቅ ብእሲ አንመካም።

## ✿ምዕራፍ ፶፭

ወልድ በፈቃዱ ሥጋን ተዋሐደ። በክርስቶስ እናምናለን። ከአብ የተገኘ ቃል እኛን ለማዳን ሰው ሆነ።

## ✿ምዕራፍ ፶፮

ከአብ የተገኘ ቃል ወልድ ዋሕድ ይባላል። ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ መላእክትም ሰዎችም ይሰግዱለታል። ቃል ክብርነቱ ለተዋሐደው ሥጋ ነው። ወክበረ ከመ ሰብእ። ሰው እንደመሆኑ ከበረ። በባሕርየ መለኮቱ ግን ከበረ አይባልም። ጥንቱንም ክቡር ነውና። ከአብ ባሕርይ የተገኘ ቃል ሰው ሁኖ ስለሁሉ ደሙን አፍስሷል።

## ✿ምዕራፍ ፶፯

የባሕርይ አምላክ ለሚሆን ለክርስቶስ መድኃኒት መባል ይገባዋል። ቃል ሥጋን በአምላክነት ክብር አከበረው። ሥጋ በተዋሕዶተ ቃል በአምላክነት ክብር ከበረ።

## ✿ምዕራፍ ፶፰

ሁሉ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። ክርስቶስ ሁሉን በመግዛት ከአብ ጋር አንድ ነው።

## ✿ምዕራፍ ፶፱

ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው። ፍጹም ሰውም ነው።

## ❁ምዕራፍ ፷

ብዙ ምእመናን በክርስቶስ አምነው ለሰማዕትነት በቁ።

❁ምዕራፍ ፷፩

አንዱ መልአክ አንዱን መልአክ አያዘውም አይገዛውም። ለእግዚአብሔር ግን ሁሉ ይታዘዛል። የባሕርይ ምስጋና ለመለኮት የሚገባ ነው። የአብ አካላዊ ቃል ሰውም ቢሆን አምላክነቱን አልለቀቀም።

❁ምዕራፍ ፷፪

ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ የሰውን ሕሊና (ሐሳብ) ሁሉ ያውቃል። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በመለኮት አንድ ነው።

❁ምዕራፍ ፷፫

አብን ማወቅ ወልድን ማወቅ ነው። በዓይነ ልቡናችን እንመርምር።

❁ምዕራፍ ፷፬

ክርስቶስን ከትንሣኤ አስቀድሞ ምንም በግዘፍ ብናውቀው ከትንሣኤ በኋላ በግዘፍ እንዳለ አናውቅም። ሥጋ ከተዋሕዶ በኋላ የመለኮት ክብር ሥልጣን ሁሉ በተዋሕዶ ገንዘቡ ነው። እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ አስተማረ።

❁ምዕራፍ ፷፭

ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደ ክርስቶስ ወልደ እጓለ እመሕያው (የሰው ልጅ) ተባለ። ይኸውም የባሕርይ አምላክ ነው።

❁ምዕራፍ ፷፮

ክርስቶስ ሕይወት ወሀቤ ሕይወት (ሕይወትን የሚሰጥ) እንደሆነ እንናገራለን። የክርስቶስ ሥጋ የክርስቶስ ደም ያድናል።

❁ምዕራፍ ፷፯

ቃል ያልተለወጠ ሥጋን ተዋሕዷል። ክርስቶስን ከጌትነት ልዩ ነው የሚል ሐሰተኛ መምህር ነው። ኢየሱስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ያመነ ሰው ዓለምን ድል ይነሣል።

❁ምዕራፍ ፷፰

ክርስቶስ ሁለንተናው ሕይወት እንደሆነ ያስረዳ ዘንድ አልዓዛርን በቃሉ አስነሣው። ወለተ ኢያኢሮስን እጇን ይዞ አስነሣት። የቃል ከሥጋ መዋሐድ በኩነት ነው እንጂ በኅድረት አይደለም። ክርስቶስ በሥራው ሁሉ አብን መሰለው። ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ሥጋ አብን መስሎ ተገኘ። በክርስቶስ ድነናል ከብረናል። ዐዋቆች ሁነናል።

## ምዕራፍ ፳፱

በእርሱ (በክርስቶስ) ደም፣ በእርሱ ሞት፣ በእርሱ ሰው መሆን እንጂ በሌላ ዓለም ይድን ዘንድ ባይቻል በፈቃዱ ሰው ሆነ። አሁንም የምንድን በክርስቶስ ነው። ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ከሞት ወደሕይወት መለሰን። በኦሪት የነበረውን ፍዳ መርገም የክርስቶስ ሞት አጠፋልን። የክርስቶስ ሕማሙ ሞቱ ለዓለም መድኃኒት ሆነ።

## ምዕራፍ ፴

በክሕደት የነበሩትን የክርስቶስ ደም አቀረባቸው። በፍዳ ተይዘን ለነበርን በሥጋው በደሙ ድኅነት ተሰጠችን። በኦሪት የነበረ ፍዳ መርገም በክርስቶስ ጠፋልን። የክርስቶስ ሕማሙ ሞቱ የዓለሙ መድኃኒት ሆነ። ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ በመሆኑ በሥጋው በደሙ አከበረን። በሥጋው በደሙ አዳነን። በሞቱ ሞትን አራቀልን።

## ምዕራፍ ፴፩

ክርስቶስ ስለእኛ ሞተልን። በሥጋ ስለእኛ መከራ ተቀበለ። የሁሉ ቤዛ አድርጎ ሥጋውን ለሞት ሰጠልን። በባሕርዩ ሕማም ሞት የሌለበት ቃል በሥጋ ታመመ። በመለኮቱ ሕማም የሌለበት በሰውነቱ ግን የታመመ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው። ታሞ ሙቶ ዓለሙን ማዳን ለእግዚአብሔር ይገባዋል።

## ምዕራፍ ፴፪

የሚዋጋን ፈቃደ ሥጋ በክርስቶስ ጠፋልን። የኃጢአት ሥራ ሁሉ በእርሱ ጠፋ። የቃል ሰው መሆን ያማረ ነው። ቃል ሥጋን እንደተዋሐደ የተናገርነው ነገር ያማረ የተወደደ ነው። ከአብ ባሕርይ የተገኘ ቃል በባሕርየ መለኮቱ ያይደለ በሥጋ ታመመ። የታመመች የሞተች ሥጋ የእርሱ ገንዘብ ናትና። በክርስቶስ ትንሣኤ እናምናለን።

## ምዕራፍ ፴፫

ቃል ሥጋን ስለተዋሐደ የባሕርይ አምላክነቱን አልለቀቀም። ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ ባዕለ ጸጋ ሲሆን በሥጋ ነድየ ተባለ። የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ እኛን የሚያከብር ክቡር ፍጹም አምላክ ነው። ሰው እንደመሆኑ ነድየ ተትሕተ ተባለ። በእርሱ ንዴት እኛ እንከብር ዘንድ ልዑል ሲሆን ተትሕተ ተባለ። በእርሱ ሕማም ሞት እኛ እንድን ዘንድ ሕያው ሲሆን ሞተ ሐመ ተባለ።

## ምዕራፍ ፴፬

ክርስቶስ እንደኛ ያለ ዕሩቅ ብእሲ አይደለም። ሰው የሆነ አምላክ አምላክ የሆነ ሰው ነው እንጂ። ቃል በሥጋ ከእመቤታችን ተወለደ።

### ምዕራፍ ፷፭

ክርስቶስ ከሁለት ተገኝቶ አንድ የሆነ ነው:: ቃል አብን በመምሰል በመተካከል ያለ እንደሆነ ዕወቅ:: የባሕርይ አምላክ እርሱ ሰው ሆነ:: ሥጋን በአምላክነት ክብር አከበረው:: የሥጋ ባሕርይ ከበረ ሊሉ ይገባል:: የቃል ባሕርይ ከበረ ሊሉ አይገባም:: ክርስቶስ በኵረ ትንሣኤ ነው:: አንዱ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው ፍጹም ሰው ነው::

### ምዕራፍ ፷፮

ዋሕድ ቃል ከአብ ጋራ እግዚአ ኵሉ እንደሆነ እናምናለን:: ሰው ቢሆን ወራሲ ተባለ:: በቃል ክብር መክበር ለሥጋ ተገባው:: የቃል ክብር ለሥጋ ክብር ሆነው:: ክርስቶስ ሰው እንደመሆኑ በሥጋ ከበረ ተባለ:: የሃይማኖት ፍጻሜ በክርስቶስ ማመን ነው::

### ምዕራፍ ፷፯

ቃል ዓለምን የፈጠረ የባሕርይ አምላክ ሲሆን በሥጋ መጣ ማለት ሥጋን ተዋሐደ:: ሰውም ቢሆን ከጌትነቱ አልተለየም::

### ምዕራፍ ፷፰

ሥጋ የተገኘ ከእመቤታችን ሲሆን ክርስቶስን ከሰማይ የወረደ እንጀራ ለምን አለው? ከተባለ ሥጋ ከሰማይ የወረደ የቃል ገንዘብ ሆኗልና ነው:: ዘዚኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል:: የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆነ:: ወእንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ:: የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆነ:: ሙሴ የሰቀለው የነሐስ እባብ የክርስቶስ ምሳሌ ስለነበር ያየው ሁሉ ይድን ነበር::

### ምዕራፍ ፷፱

ወልድ በባሕርዩ ከአብ ባሕርይ ተወለደ:: ስለዚህም አብ ለወልድ የባሕርይ አባቱ ነው:: ክርስቶስ ከሥጋ ባሕርይ ከመለኮት ባሕርይ ተገኝቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደሆነ ይታወቃል::

### ምዕራፍ ፸

ሐዋርያት በእግዚአብሔር ስም አስተማሩ እንጂ በዕሩቅ ብእሲ ስም አላስተማሩም:: በክርስቶስ አምነን እንከብራለን::

### ምዕራፍ ፸፩

ሰው ሳይሆን አስቀድሞ ቃልን ክርስቶስ የሚለው አልነበረም:: ሰው በሆነ ጊዜ ክርስቶስ ኢየሱስ ተባለ እንጂ::

### ምዕራፍ ፸፪

አባቶቻችን የክርስቶስ ሕግ የአብ ሕግ እንደሆነ አስተማሩን:: በአብ ማመን በክርስቶስ ማመን ነው::

### ምዕራፍ ፹፫

በሥጋ እንደእኛ ሰው የሆነ አምላክ ነው፡፡ ክርስቶስን ሰው የሆነ አምላክ ነው ብለን እናከብረዋለን፡፡

### ምዕራፍ ፹፬

በአብ ያመነ በክርስቶስ ያመነ ነው፡፡

## 🌹ጳላድዮስ

### ምዕራፍ ፩

ይህንን ድርሳነ ቄርሎስ ወጳላድዮስ ጳላድዮስ እየጠየቀ ቄርሎስ እየመለሰ ተናግረውታል፡፡ ጳላድዮስ የቄርሎስ ደቀመዝሙር ነው፡፡ የመጻሕፍትን ትምህርት ማንም ማን አይሰለችም፡፡ የመጻሕፍት ትምህርት ለማንም ለማን አይሰለችም፡፡ ይልቁንም ጥበብን ለተማሩ ሰዎች አይሰለችም፡፡ የነፍስ ምግብ ትምህርት ነው፡፡ ሥጋው ደሙ ኃይለ ነፍስን ያጸናል፡፡

### 🌹ምዕራፍ ፪

አርዮስ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ ይላል፡፡ ንስጥሮስም ፍጡር ይላል፡፡ በሥጋ እንዳይል አያዋሕድም፡፡ ካላዋሐደ በመለኮቱ ያሰኝበታልና፡፡ የአርዮስም የንስጥሮስም ነገራቸው ሐሰት ነው፡፡ መጻሕፍት በተናገሩት ነገር ያልጸና ንስጥሮስ ሐዲስ ከይሲ እየተባለ ይጠራል፡፡

### 🌹ምዕራፍ ፫

አማኑኤል አምላክ ወሰብእ ነው፡፡ በሥጋ ከድንግል ማርያም የተወለደው ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ ነው፡፡

### 🌹ምዕራፍ ፬

በመለኮት ውላጤ (መለወጥ) የለበትም፡፡

### 🌹ምዕራፍ ፭

አካላዊ ቃል መለወጥ ሳይኖርበት፣ መቀላቀል ሳይኖርበት ባሕርዩን ከሥጋ ባሕርይ አካሉን ከሥጋ አካል አዋሐደ፡፡ ከአዳም ባሕርይ የተገኘ ሥጋን ተዋሐደ፡፡ ይህም ሥጋ ነፍስ ያለው ሥጋ ነው፡፡ ቃል ነፍስ ሕይወቱ የምትሆን ሥጋን ተዋሐደ፡፡ የባሕርይ አምላክ ሲሆን ሰው ሆነ፡፡

### 🌹ምዕራፍ ፮

ክርስቶስ ፍዳ ኃጥኣንን ለማጥፋት ኃጥእ ሳይሆን ኃጥእ ተባለ፡፡ ቃል ሥጋን ተዋሕዶ በሥጋ

የሰውነትን ሥራ ሠራ::

## 🌹ምዕራፍ ፯

ክርስቶስ መርገምን ያጠፋ ዘንድ ርጉም ሳይሆን ርጉም ተባለ:: ሰው በሞተ ጊዜ አራቱ ባሕርያት ይለያዩበታል:: ጌታ በፈቃዱ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ግን አራቱ ባሕርያት አልተለያዩበትም::

## 🌹ምዕራፍ ፰

ቃል ልዑል ሲሆን በሰውነቱ ተትሕተ ተባለ::

## 🌹ምዕራፍ ፱

ቅድመ ዓለም የነበረ ቃል በሥጋ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደተወለደ የጎላ የተረዳ ነው::

## ✿ምዕራፍ ፲

ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ የሕይወት ቃል ገንዘብ በመሆኑ አዳነን:: ደሙም ከኃጢአታችን አነጻን:: ወበብዕለ ዚኣሁ አብዐሎ እግዚአብሔር ቃል ለሥጋ:: በማይመረመር በማይታወቅ ተዋሕዶ ሥጋን በባሕርይ ክብሩ አከበረው:: ሥጋ ከሰማይ አልወረደም:: ቃል አምላክ ሲሆን ሰው ሆኗልና ከቃል ጋር ስለተዋሐደ ወረደ ይባላል እንጂ::

## ✿ምዕራፍ ፲፩

ቃል አምላክ ሲሆን ሥጋን ተዋሐደ:: በጌትነት ክብር ያከብረን ዘንድ ስለእኛ እንደእኛ ሰው ሆነ::

## ✿ምዕራፍ ፲፪

ልጅነትን ክብርን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ:: በክርስቶስ ሰማያዊ ሆንን::

## ✿ምዕራፍ ፲፫

አካላዊ ቃል ሰው ሆኗልና የሥጋን ሥራ መሥራቱ እውነት ነው:: ከሓድያን ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋን ከቃል ቃልን ከሥጋ ይለዩታል:: እኛስ ከተዋሕዶ በኋላ ለያይተን አንናገርም:: ክርስቶስ ማለት መሢሕ ማለት ነው::

## ✿ምዕራፍ ፲፬

የሥላሴ ባሕርይ አንድ ነው:: ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ተብለው ይጠሩ ዘንድ አይገባቸውም:: ከዘርዐ ዳዊት በሥጋ ለተወለደው ለወልድ ክርስቶስ መባል ይገባዋል እንጂ::

✿ምዕራፍ ፲፭

ቃል ሥጋ ሆነ ተብሎ ተነግሯልና ክርስቶስ መባል ይገባዋል። ይኸውም በሰውነቱ ከበረ ማለት ነው።

✿ምዕራፍ ፲፯

በተዋሕዶ አንድ የሚሆን ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ ነው። ሰው እንደመሆኑ መጠን መክበር በሚገባው በሥጋ ከበረ ተባለ። ቃል በተዋሕዶ የአዳምን ባሕርይ ገንዘቡ አደረገ።

✿ምዕራፍ ፲፱

ኦሪት የክርስቶስን ተዋሕዶ ትናገራለች (በምሳሌ)። ሃይማኖታችን ደገኛና ክብርት ናት።

✿ምዕራፍ ፳

ነግሡ እግዚአብሔር በነቢያት። እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ እስራኤልን ገዛ አስተማረ። ነቢያትን ማክበር እግዚአብሔርን ማክበር ነው። ዘርዐ ዳዊት በተዋሕዶ የአምላክነትን ክብር አገኘ።

✿ምዕራፍ ፳፬

ቃል ራሱን ከሥጋ ጋር አዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ አደረገ። ቃል ባይዋሐደው ሥጋ በአምላክነት ክብር ባልከበረም ነበር። በክርስቶስ አምነን ስንጠመቅ ውሉደ እግዚአብሔር እንባላለን። ይህ የነጻነት ስማችን ነው።

✿ምዕራፍ ፳፭

ቃል ወደሥጋነት ሥጋ ወደቃልነት ተለወጠ ሊሉ አይገባም። ከመመርመር በራቀች ተዋሕዶ ሥጋና ቃል አንድ ሆኑ።

✿ምዕራፍ ፳፯

ከተዋሕዶ በኋላ ክርስቶስን አምላክ ነው ስንለው ከሥጋ ለይተን አይደለም። ሰው ነው ስንለውም ከጌትነቱ ለይተን አይደለም። ሙሴ እሳቱ ቅጠሏን ሳያቃጥላት ቅጠሏ እሳቱን ሳታጠፋው ያያት ዕፅ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌ ናት።

✿ምዕራፍ ፴፩

አብን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው፣ ከወለደው ከአብ ጋራ በሁሉ አንድ የሚሆን ቃል ራሱን ከሥጋ ጋር አዋሕዷል። ጌትነቱን ሳይለቅ የሰውነትን ሥራ ሠራ።

## ምዕራፍ ፴፩

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ያደረበት ዕሩቅ ብእሲ አይደለም።

## ምዕራፍ ፴፪

የክሕደት መመላለሻ ንስጥሮስ የመጻሕፍትን ምሥጢር አያውቅም። አካላዊ ቃል ስለእኛ እንደእኛ ሰው ሆነ።

## ምዕራፍ ፴፫

ሥጋ በኅድረት ሳይሆን በኩነት የባሕርይ ክብርን ከበረ።

## ምዕራፍ ፴፬

ዘለዓለም የነበረ ቃል ሰው ቢሆን ዘትማልም ወዮም ተባለ። ሰው ስለሆነ ወልደ ዳዊት ተባለ።

## ምዕራፍ ፴፭

የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ሐሰት አይደለም።

## ምዕራፍ ፴፮

ለቃልሰ አልቦ ዘእምቀደስዎ። ከመጻሕፍት ከመምህራን ቃልን ከበረ ያለው የለም። እስመ ቅዱስ ውእቱ በህላዌሁ። በባሕርዩ ክቡር ነውና። ሰው በመሆኑ ከበረ አለ። አምላክ እንደመሆኑ ያከብራል።

## ምዕራፍ ፴፯

ቃል ሰው ስለሆነ የሰውነት ሥራ ሁሉ ገንዘቡ ሆኗል። የሰውን ባሕርይ በተዋሕዶ አከበረው።

## ምዕራፍ ፵

አካላዊ ቃል ሰው ሆኖ ለእኛ ለሰው ልጆች የመልካም ሥራ አብነት ሆነን። በመዋዕለ ሥጋሁ ኮነነ አርአያ።

## ምዕራፍ ፵፩

ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብለን ለምናምን ሰዎች ለሰውነት የሚገቡ ቃላት የተረዱ ናቸው።

## ምዕራፍ ፵፪

በአዳም ሕግ ማፍረስ በፍዳ ተይዘን ነበር። ሞት ባመጣው ፍዳ ተይዘን ነበር። ይእዜሰ ተሐደሰ በክርስቶስ ኵሉ። ዛሬ ግን ሁሉ በክርስቶስ ታድሷል። የልጅነታችን በኩር እርሱ ነው። ክርስቶስ

ዳግማዊ አዳም እየተባለ ይጠራል።

### ምዕራፍ ፺፫

ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ብሎ ፈጽሞ መለየት አይገባም። ለቃል በተዋሕዶ የሥጋ ድካም ገንዘቡ እንደሆነ እንናገራለን። ከኃጢአት በቀር በሥራው ሁሉ ወንድሞቹን መስሏቸዋልና።

### ምዕራፍ ፺፬

ክርስቶስ በጥበብ አደገ መባሉ በሥጋ ነው። ቃል እንደኛ ያለ ሰው ሆኗልና የእኛን ገንዘብ ገንዘብ አደረገ። ነገር ግን አምላክ እንደመሆኑም ከእኛ በላይ እንደሆነ ልናውቅ ይገባል። ለቃል የሰውነት ሥራ ሁሉ በተዋሕዶ ገንዘቡ እንደሆነ እንናገራለን። ከስድቦች ሁሉ ጌታን ዕሩቅ ብእሲ ማለት ይከፋል። መለኮት በባሕርዩ አይታይም። ነገር ግን በሥጋ እንጀኛ ባለ ባሕርይ ታየ።

### ምዕራፍ ፺፭

ጳውሎስ ክርስቶስን በሥጋ ታመመ ሞተ አለ ብለን ስንናገር በመለኮቱ አልታመመም አልሞተም ብሎ ተናገረ ማለታችን ነው። ወይቤ ጴጥሮስ በእንተ ክርስቶስ ምዕረ ሞተ በእንተ ኃጢአትነ በሥጋሁ።

### ምዕራፍ ፺፮

ቃል ሰው ሆኗልና በሥጋ ታመመ። በእግዚአብሔርነቱ ኃይል ከሞት ተነሣ እንላለን። እስመ እግዚአብሔር ሥግው። ሥግው ቃል ነውና።

### ምዕራፍ ፺፯

የአብ ፈቃድና የወልድ ፈቃድ አንድ ነው። የዓለም መፈጠር ለድኅነት ነው። ክርስቶስ በኩረ ትንሣኤ በኩረ ሙታን ሆነ። በኩረ ሙታን መባሉ ለሞቱት በትንሣኤ በኩር ስለሆናቸው ነው። ወቀደሞሙ ለእለ ኖሙ እንዲል።

### ምዕራፍ ፺፰

ከሰው ወገን ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ መልሶ ከሞተ በኋላ ማስነሣት የሚቻለው የለም። ነፍሱን ከሥጋው መለየት መልሶ አዋሕዶ ማስነሣት የሚቻለው ለእርሱ ለክርስቶስ ብቻ ነው።

## ተረፈ ቄርሎስ

### ምዕራፍ ፩

በዚህ በተረፈ ቄርሎስ የሌሎች ቅዱሳን ሊቃውንት ትምህርትም አለበት። ለምሳሌ ይህን ምዕራ

ፍ ቴዎዶጦስ ዘዕንቆራ ጽፎታል። ይህም ገድለ ጊዮርጊስን የጻፈ ሊቅ ነው። ኃጢአት የነፍስ ደዌ ነው። ካህናት መክረው አስተምረው ነፍስን ከኃጢአት ያድናሉ። የከበሩ የነፍሳት ባለመድኃኒቶች መምህራን ከጥንት ጀምረው መክረው አስተምረው ምእመናንን ከኃጢአት ጠብቀው ኖሩ። የቃልን ሰው መሆን አትካድ የሥጋን አምላክ መሆንም እንዳትክድ። ቃል ሥጋን ተዋሕዶ ለአዳም መከራ ይቀበልለት ዘንድ ወደደ። ሕማም ሞት የሌለበት የመለኮት ባሕርይ ሕማም ሞት የሚስማማው ሥጋን ተዋሕዷል።

### ምዕራፍ ፪

ዘቄርሎስ፦የሐዋርያት ትምህርታቸው ሕይወት የሚገኝበት ትሞህርት ነው። ዋሕድ ቃል ሰው የሆነ ጌትነቱን ሳይለቅ ነው።

### ምዕራፍ ፫

ዘሳዊሮስ ዘፊርግያ፦ የክርስቶስን የአምላክነቱን ምስክር ከነገሩ ይልቅ በሥራው ፈጽመን እንረዳለን። እርሱ ጥቂት ይናገራል ብዙ ሥራ ይሠራል። ኅዳጠ ይትናገር ወዐበይተ ይገብር።

### ምዕራፍ ፬

ዘአቃቅዮስ፦ የክርስቶስ ፍቅር አንድነት ወገኖቹ በሚሆኑ በምእመናን ጸንቷል። ክርስቶስ ስለእኛ በፈቃዱ በሥጋ ታመመ።

### ምዕራፍ ፭

ዘዮብላንዮስ፦ ፍጥረታትን የፈጠረ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። አለኝታችን ሰው በሆነ በእግዚአብሔር ነው እንጂ በዕሩቅ ብእሲ አይደለም። እኛን አማልክት ዘበጸጋ ያደርገን ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ።

### ምዕራፍ ፮

ዘቄርሎስ፦ ክርስቶስ በከበረ ደሙ አዳነን።

### ምዕራፍ ፯

ዘቄርሎስ፦ የሁላችን መድኃኒት በሚሆን በክርስቶስ ፍቅር ሁልጊዜ ጸንተን ልንኖር ይገባል። ክርስቶስ በአገልጋዮቹ በሊቃውንት አድሮ ያሸንፋል።

### ምዕራፍ ፰

ዘቴዎዶጦስ፦ ጌታ ወደ ግብጽ የተሰደደው ፈርቶ አይምሰልህ። አላ ነጽር ከመ ጕየተ ሕፃን አጕየዮ ለዲያብሎስ። የጌታ ስደት ዲያብሎስን ከሰው ልቡና አስወጥቶ ሰደደው እንጂ። ያለመከራ ክብር አይገኝም። ስለዚህ ስለሃይማኖታችሁ መከራን ተቀበሉ።

## ምዕራፍ ፲፭

ዘኤጺፋንዮስ፦ ምእመናን ስለየዋሕነታቸው ርግብ ይባላሉ:: አብ በአካሉ ፍጹም ነው:: ወልድም በአካሉ ፍጹም ነው:: መንፈስ ቅዱስም በአካሉ ፍጹም ነው:: በባሕርይ አንድ ናቸው:: ወልድ ከአብ የተወለደ የባሕርይ ልጅ ነው:: በአንድነት በሦስትነት ለዘለዓለም ጸንተው ይኖራሉ:: ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር ብቻ ነበረ እንጂ ሌላ አካል አልነበረም:: አካላዊ ቃል ከባሕርዩ ሳይለወጥ ሰው ሆነ:: መለኮት የተዋሐደው ሥጋ ክብርን ያስገኛል::

## ምዕራፍ ፲፮

ክርስቶስ እውነተኛ ሰው መሆኑን ለማስረዳት ተራበ:: በጠቅላላው የሰውነትን ሥራ ሠራ:: እስመ ክርስቶስ በእንቲአነ ሐመ በሥጋሁ:: ክርስቶስ ስለእኛ በሥጋ መከራ ተቀብሏል:: ወዘእንበለ ሕማም ነበረ በመለኮቱ:: በመለኮቱ ሕማም የሌለበት ሆኖ ኖረ:: ቅዱስ ጳውሎስ ለእመሂ አእመርናሁ ለክርስቶስ በሥጋ አላ እምይእዜ ኢነአምሮ:: ክርስቶስን ከትንሣኤ አስቀድሞ ምንም የግዘፍ ሥራ ሲሠራ ብናውቀው ከትንሣኤ በኋላ የግዘፍ ሥራ ሲሠራ አናውቀውም ብሎ መስክሯል:: እንዲህ ስላለ ሥጋን ከመለኮት ለይቶ አይደለም:: ከትንሣኤ በኋላ በአምላክነት ግብር ጸንቶ መኖሩን ይነግረናል እንጂ:: በባሕርዩ ሕማም የሌለበት አምላክ በሥጋ ታመመ::

## ምዕራፍ ፲፯

ቃል ሥጋ ሆነ ሲባል መለኮቱን ሥጋ ወደመሆን ለወጠ ማለት አይደለም:: መለኮት ሥጋን በተዋሕዶ ገንዘብ አደረገ ማለት ነው እንጂ::

## ምዕራፍ ፲፰

ዘጽርቅሎስ፦ ድንግል ማርያም የዳግማዊ አዳም የክርስቶስ እናት ናት:: ትስብእትና መለኮት አንድ የሆኑባት ናት:: በዕፀ ጳጦስ፣ በጸምር ትመሰላለች:: ክርስቶስ በሰማያዊ ልደቱ እናት በምድራዊ ልደቱ አባት የለውም::

## ምዕራፍ ፲፱

ሁሉ በአንድ በአዳም ምክንያት ፍዳ ደርሶበት ነበር:: ዳግማዊ አዳም የተባለ ጌታችን ለእኛ ቤዛ ሆኖ ለሕማም ለሞት ተሰጥቷል:: በለበሰው ሥጋ ታሞ ሙቶ አዳነን:: ክርስቶስ ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ እኛ ልናቀርበው የሚገባንን ልመና ለእኛ አብነት ለመሆን የባሕርይ አባቱ ወደሚሆን ወደአብ አቀረበ:: ለሰው ያደረገውን ፍቅሩን ዕወቅ:: አምላክ ከሥጋ ተለይቶ መከራ አልተቀበለም:: አምላክ ሲሆን ሰው ሆኗልና በሥጋ መከራ ተቀበለ እንጂ:: በሥጋ መከራ የተቀበለ እርሱ በመለኮቱ ያድናል:: እንደሰውነቱ በእናቱ ክንድ የተወሰነ እርሱ በምልዐት ይኖራል::

## ❁ምዕራፍ ፳

ዘሳዊርያኖስ፦ አስቀድሞ ያልመረመሩትን ነገር ድንገት ከአንደበታቸው አውጥተው የሚናገሩ ሰዎች ዐላዋቆች ይባላሉ። ሃይማኖት የነፍስ መጽኛና የሕይወት መሠረት ናት። ሥርውሰ እንተ ሃይማኖት ሕይወተ አብ ውእቱ። የሃይማኖት ጥንቱ የአብ ባሕርይ ነው። ሥላሴ እንተ እምቅድመ ዓለም ሀለወት። ሦስትነት ዓለም ሳይፈጠር የነበረች ናት። ለመኖሯ ጥንት ፍጻሜ የለውም። መለወጥም የለባትም። ኀልፈት የለባትም። ቀድሞ እንደነበረች ለዘለዓለም ጸንታ ትኖራለች። ሃይማኖት አብን ወላዲ አሥራፂ፣ ወልድን ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ ብሎ ማመን ነው።

## ❁ምዕራፍ ፳፩

ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ናቸው። አብ ሰማይን ፈጠረ ስንል ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ አይደለም። የእግዚአብሔር ሕግ ለኃጢአት ከመገዛት ነጻ ያደርጋል።

## ❁ምዕራፍ ፳፪

ወልድ ወላዲ ከሆነ ከፍጹም አብ የተገኘ ፍጹም ነው። ከእግዚአብሔር የተገኘ እግዚአብሔር ነው። ከሥላሴ ምንም ምን ፍጡር የለም። የሚያዝ የሚታዘዝ የለም።

## ❁ምዕራፍ ፳፫

የመልከጼዴቅ የዘር ሐረግ የሚከተለው ነው። ካም ከነዓንን፣ ከነዓን ሴዱን፣ ሴዱ ሳሌምን፣ ሳሌም ሔሴልን፣ ሔሴል መልከጼዴቅን ይወልዳል። ከዓይነ ልቡናችሁ ድንቁርናን አርቃችሁ እውነተኛውን ነገር ሹ መርምሩ። እስራኤል ማለት እግዚአብሔርን የሚያየው እግዚአብሔርን የሚያውቀው ልቡና ማለት ነው።

## ❁ምዕራፍ ፳፬

በመንፈስ ቅዱስ የከበርን እኛ ፈጥኖ ለሚያልፍ ለዚህ ዓለም ክብር መድከምን መመካትን እናርቃለን። ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ እውነት የሚፈርድ የፍቅር ባለቤት ነው። ለመልከጼዴቅ የሌዋውያን ትውልድ በተጻፈበት መጽሐፍ እናት አባት ለዘመኑ ጥንት ለአነዋወሩ ፍጻሜ የለውም። (በመጽሐፉ አልተጻፈም ለማለት ነው)።

## ❁ምዕራፍ ፳፭

መልከጼዴቅ ደግ ሰው ነበር። የልዑል እግዚአብሔር አገልጋይ ነበር። በዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን በማመስገን ኅብስቱን ወይኑን መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀርብ ነበር። ክርስቶስ በፈቃዱ መከራን እንደተቀበለ እናምናለን።

## ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን!

# ነገረ ክርስቶስ

**ይህ ክፍል ከድርሳነ ቄርሎስ ወጳላድዮስ ወተረፈ ቄርሎስ የተወሰደ አይደለም ከተለያዩ መጻሕፍት ራሴ ያዘጋጀሁት ነው፡፡**

## የሕይወት ምርኮ

በቅድሚያ እንኳን ለበዓለ ዕርገተ ክርስቶስ አደረሳችሁ፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ምርኮን ማረከን፡፡ ዐረገ ውስተ አርያም ዔዊወከ ዔዋ እንዲል፡፡

ምርኮን ማርከህ

ወደ ሰማይ ዐረግህ

ሁለት ዓይነት ምርኮዎች አሉ፡፡ እነዚህም የሕይወት ምርኮና የጥፋት ምርኮ ናቸው፡፡ የጥፋት ምርኮ የሚባለው የእስራኤላውያን በባቢሎናውያን መማረክ ነው (፩ኛ ዜና መዋ.፱፥፩)፡፡ እስራኤላውያን ኃጢአትን ቢያበዙ በባቢሎን ተማረኩ፡፡ በዚህኛው የምርኮ ሕግ ተማራኪዎች በማራኪዎች ፈቃድ ይኖራሉ፡፡ ተማራኪዎች ነጻነት ሳይኖራቸው በባርነት ይኖራሉ፡፡ ውሉደ አዳም እኛም በኃጢአት ምክንያት ልጅነትንና ገነትን አጥተን በዲያብሎስ አገዛዝ በሲኦል እስር ቤት እንኖር ነበር፡፡ እስራኤል ዘሥጋ የእስራኤል ዘነፍስ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ባቢሎን የሲኦል ምሳሌ ነው፡፡ ባቢሎናውያን የአጋንንት ምሳሌ ናቸው፡፡ እስራኤላውያን በዘሩባቤል አማካኝነት ከባቢሎን ወጥተዋል፡፡ ዘሩባቤል የጌታ ምሳሌ ነው፡፡ በጠቅላላው በጦር ተሸንፈው፣ በገንዘብ ተገዝተው የሚማረኩት ምርኮ የጥፋት ምርኮ ይባላል፡፡ ዲያብሎስ በተንኮሉ ማርኮን የዲያብሎስ ምርኮኞች ሆነን ለ5500 ዘመን ኖረን ነበር፡፡

የነጻነታችን አክሊል፣ የሕይወታችን መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እለ ውስተ ሲኦል ፃኡ፡፡ በሲኦል ያላችሁ ውጡ፡፡ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ፡፡ በጨለማ ውስጥ የምትኖሩ ብርሃን እኔ ሰው ሆኜ አድኛችኋለሁና ውጡ አለን፡፡ በዲያብሎስ አገዛዝ የነበርን እኛን እርሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሲኦል አወጣን፡፡ የጥፋት ምርኮን ያይደለ የሕይወት ምርኮን ማረከን፡፡ በሕይወት ምርኮ ተማራኪዎች ያለፈቃዳቸው በግዴታ የሚያደርጉት ሥራ የለም፡፡ ማራኪውም መልካም ፈቃዳቸውን ይፈጽምላቸዋል፡፡ በጥፋት ምርኮ የሚጠቀመው ማራኪው አካል ነው፡፡ በሕይወት ምርኮ ግን ተጠቃሚው ተማራኪው ነው፡፡ ጌታ እኛን ወደ እርሱ ሕይወት ሲማርከን ለእርሱ የተጨመረለት ነገር የለም፡፡ እርሱ በባሕርይው ፍጹም ነውና፡፡ እኛ ግን በእርሱ በመማረካችን ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከባርነት ወደ ልጅነት ተሸጋገርን፡፡ የጌታ ዕርገት ለጻድቃን ዕርገት በኩር ነው፡፡ ዐርገ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሓን እንዲል፡፡ እርሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዲስ ተፈጥሮ፣ ለትንሣኤ፣ ለዕርገት በኵር ሆነን፡፡

"ወእንዘ ይባርኮሙ ተረኀቆሙ" እንዲል ጌታ ከትንሣኤ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ (ሉቃ.፳፬÷፶፩)፡፡ ወደሰማይም ዐርጎ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ (ማር.፲፮÷፲፱)፡፡ የእግዚአብሔር ቀኝ የተባለው አምላካዊ ሥልጣን ነው፡፡ በዚህ ምድር ሲመላለስ ይራብ ይጠማ

ነበር። ከትንሣኤ በኋላ ግን ባለመራብ ባለመጠማት አምላካዊ ግብር ጸንቶ ኖሯልና በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ አለ። መጋቢት ፳፱ ቀን በዕለተ ፅንሰቱ ቃል ሥጋ ሲሆን ለቃል ርደት ሲነገር ለሥጋ ዕርገት ይነገራል። መተርጉማን ሃይማኖተ አበው ምዕራፍ ፲፯ን ሲተረጉሙ የቃል ዕርገት በአርባ ቀን የሥጋ ዕርገት በማኅፀን ይላሉ። የሥጋ ዕርገት በማኅፀን መባሉ ሰው አምላክ መሆኑን ያሳውቃል። በዚህ አንፃር የቃል ርደት ሲነገር አምላክ ሰው ሆነ ማለት ነው። ሥጋ በማኅፀን ዐረገ መባሉ የቃልን ገንዘብ ገንዘብ በማድረጉ በድንግል ማኅፀን ተወስኖ ሳለ በኪሩቤል ጀርባ መቀመጡን ግዙፍ ሳለ መርቀቁን መግለጥ ነው። ግዙፍነትን ሳይለቅ ርቀትን ገንዘብ በማድረጉ የርቀት ዕርገት ይባላል። የቃል ዕርገት በአርባ ቀን ማለት በሁሉ ምሉእ የሆነ ቃል ሰውነትን በማኅፀን ገንዘብ በማድረጉ በሥጋ ርስት ወደሰማይ መውጣቱን መግለጽ ነው። ይህ ዕርገት የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገት ይባላል። በድጋሚ እንኳን አደረሳችሁ።

## ሃይማኖት

ስለ ነገረ ክርስቶስ ለመነጋገር መሠረታችን የፈጣሪ መኖር ነው። በፈጣሪ ህልውና ዙሪያ ብዙ አስተያየቶች አሉ። ጠቅለል ስናደርጋቸው ግን ሦስት ናቸው። እነዚህም:-

1) ፈጣሪ የሚባል የለም

2) ፈጣሪ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል

3) ፈጣሪ አለ

የሚሉት ናቸው። ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተጠቀሰውን የሚደግፉ የራሳቸውን አመለካከት ለመደገፍ የሚያቀርቡት የየራሳቸው አመክንዮ አላቸው። የአመክንዮአቸው ጥንካሬ ግን ደካማ ሆኖ ይገኛል። Full of fallacy ሆኖ ይገኛል። አንዳንዶች ለድምዳሚያቸው መነሻ ያደረጉት ሐሳብ (premise) የተሳሳተ ስለሆነ ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ (Conclusion) አድርሷቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ መነሻ ሐሳቦቻቸው ትክክል ቢሆኑም የተሳሳተ ቅደም ተከተልን (Wrong arrangement) መሠረት አድርገው ከተሳሳተ ድምዳሜ ይደርሳሉ። በእርግጥ የትክክለኙነት መለኪያው ምንድን ነው? የሚለውም ለብቻው በስፋት የሚታይ ነው።

አንድን ነገር አለ ወይም የለም ለማለት የሚያበቃን አእምሯችን ነው። አእምሮ ደግሞ ዕውቀትን በተፈጥሮ ካገኘው በተጨማሪ በስሜት ሕዋሳት አማካኝነት ከተፈጥሮ ጋር ባለው ግንኙነት የሚያውቃቸው ዕውቀቶች አሉት። እነዚህ ዕውቀቶች ግን አንድን ነገር በትክክል ይገልጻሉ ወይንስ አይገልጹም? የስሜት ሕዋሳቶቻችን ለአእምሯችን የሚያስተላልፉት መልእክትስ ትክክለኛነቱ በምን ይረጋገጣል? ለምሳሌ አንድ ቀጥ ያለን ዱላ በውኃ ውስጥ ስንመለከተው ጠመም ያለ ይመስላል። በዓይናችን አማካኝነት አእምሯችን የተረዳው ነገር ቢኖር ጠመም ያለ እንደሆነ ነው። ከውሃ ወጥቶ ሲያዩት ደግሞ ቀጥ ያለ ነገር እንደሆነ ይረዳል። ታዲያ ስለዱላው ትክክለኛው ነገር ምንድን ነው? አንዳንዱ ዱላው ቀጥ ያለ ነው ጠመም ያለ የመሰለን በውኃው ምክንያት ነው የሚል ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ከውኃው ሲወጣም ከሌሎች

ተጽእኖ ምሳሌ አየር፣ ሙቀትና ከመሳሰሉት ነጻ ስላልወጣ ቀጥ ያለ ነው ለማለት ከእነዚህ ነገሮች ነጻ የወጣ መሆን አለበት። ይህን ሁሉ የምንለው አእምሮ ራሱ አንድን ነገር ለመበየንና የበየነው ነገር ቋሚ ትክክል (Always true) የሆነ ነገር ሳይሆን እንደሚገኝ በጥቂቱ ለማመልከት ነው።

አእምሮ ከስሜት ሕዋሳት መረዳት በላይ የሆኑ ጉዳዮችን እንደሌሉ ሊበይን ይችላል። scientifically ጆሮ የሌላቸው ሌሎች የስሜት ሕዋሳቶች ግን ምሳሌ ዓይን አፍንጫና የመሳሰሉት ያላቸው ፍጥረታት እንዳሉ ይነገራል። ጆሮ ለሌለው ፍጥረት ዓለም በጩኸት ቢደበላለቅ የድምፅ ህልውና ለእርሱ ውሸት ሊመስለው ይችላል። በእርግጥ እግዚአብሔርም ባሉን የስሜት ሕዋሳቶቻችን ሁሉ የማይረዳ ከስሜት ሕዋሳቶቻችን ሁሉ በላይ ነው። ሊቅ ባስልዮስ "ለእመ ተጋብኡ ኀቡረ መላእክት ወሊቃነ መላእክት በበዘመዶሙ ዘምስለ ኵሎሙ ፍጡራን አሐተኔ ኢይክሉ ይርከቡ ኀዳጠ እምአእምሮተ ህላዌሁ ለእግዚአብሔር" እንዳለ በሃይማኖተ አበው እንኳንስ እኛ ቅዱሳን መላእክት ሁሉ በአንድነት ሆነው ቢመረምሩት ባሕርይው ከመመርመር በላይ ነው። በስሜት ሕዋሳት ካልተረዳነው የሚባል አይደለም። ፈጣሪ የለም የሚሉ አካላት ፈጣሪን ምን ዓይነት አድርገው ፈልገው አጡት??? እግዚአብሔርን የለም ለማለት በማንነቱ ፈልጎ ማጣት አይቀድምም ወይ? ረቂቅ ነኝ እያለ ግዙፍ ነገር ፈልገው ካጡት መጀመሪያውንም የፈለጉት እግዚአብሔርን ሳይሆን በኅሊናቸው ራሳቸው የፈጠሩትን ፈጣሪ ነው። አልታይም፣ አልዳሰስም እያለ የሚታይ የሚዳሰስ ነገር ፈልገው ካጡ ችግሩ የራሳቸው ነው። ፈጣሪ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል የሚሉት አካላት ደግሞ አለ እንዳንል በየትኛውም የስሜት ሕዋሳቶቻችን አልተረዳነውም። የለምም እንዳንል የስሜት ሕዋሳቶቻች ወሰን አለባቸው የሚሉ ማዕከላውያን ናቸው። በዚህ ዙሪያ በተለይም በTheoretical Philosophy ክፍሎች ማለትም በMetaphysics እና በGnosiology የሚነሱ የተለያዩ ሀሳቦች አሉ። ሁሉንም ሐሳቦች ግን በተሰጠን አእምሮ ስንመረምራቸው እዚህ ግባ የሚባል አሳማኝ ነገር የላቸውም። በእርግጥ ሳይመረምር ሳያላምጥ የሚውጥን ሰው በቀላሉ ሊማርኩት ይችላሉ። የኦሾ ተራ ፍልስፍና የሚያንበረክከው ትውልድ እነዚህ በጣም ሊከብዱት ይችላሉ። እያንዳንዳቸውን እየሞገትን እስከ ፍጻሜው ለማየት እንሞክራለን።

እኛስ እግዚአብሔር አለ የምንለው ምንን መሠረት አድርገን ነው? የሚለውን ማወቅ ግን ከሁላችንም ይጠበቃል። ፈጣሪ አለ ያልነው በስሜት ሕዋሳቶቻችን መርምረን ደርሰንበት አይደለም። ከስሜት ሕዋሳት በላይ ነውና። ነገር ግን ለስሜት ሕዋሳቶቻችን ቅርብ በሆነ መንገድ በዘፈቀደ በዘንክል (እርሱ በወደደው እኛ ልናየው በምንችለው መጠን) በተለያየ አምሳል ተገልጾ አምላካዊ ሥራዎችን ሠርቶ በማሳየት ተገልጦልናል። ይህ ብቻ አይደለም ሰው ሆኖ አምላካዊ ሥራዎችን እየሠራ ዓለም አየው። እነዚህን ማስረጃዎች ይዘን የፈጣሪን መኖር እናምናለን። ሰው ሆኖ ክርስቶስ የተባለው ዓለምን ቀድሞ የፈጠረው ነው። ለዛሬ ይችን ብቻ ገልጬ ልለፍ። ይህ ነገረ ክርስቶስ ምዕራፍ ፩ በዋናነት በፍልስፍና መነሻነት ክርስቶስን ለሚክዱ ምላሽ የሚሰጥ ነው። በውስጡም 120 ክፍሎች ይኖሩታል። ከዚያ ምዕራፍ ፪ ብሉይ ኪዳንን መሠረት አድርገን 300 ክፍሎችን እናያለን። ምዕራፍ ፫ መጻሕፍተ ሊቃውንትንና መጻሕፍተ መነኮሳትን መሠረት አድርገን ከተማማርን በኋላ ወደ ሌላ የትምህርት ርእሰ ጉዳይ

እንገባለን። ምዕራፍ ፩ ሐዲስ ኪዳንን መሠረት አድርገን 343 ክፍሎችን ተማምረናል። እርሱን በPDF በቴሌግራም ቻናሌ ታገኙታላችሁ። በዓመት ውስጥ ለመጨረስ እንዲያመቸን በቀን ብዙ ክፍሎችን ልለቅ እችላለሁ።

በነገራችን ላይ የክርስትና ትምህርት ፍልስፍናን የሚያንበረክክ እንጂ ከፍልስፍና ያነሰ አይደለም። በአመክንዮ ለሚያጣጥሉን ሰዎች ከእነርሱ አመክንዮ በላይ የሆነ አመክንዮ አለን። ይህ ብቻ አይደለም ከእነርሱ በተሻለ አመክንዮ ለማይመልሳቸው ጥያቄዎች በቂ ምላሽ የሚሰጥ እምነትም አለን። አእምሮ ሊመረምረው የማይቻለውን ጉዳይ በእምነት እንመረምረዋለን። ከኅሊና በላይ ያሉ ጉዳዮችን በሃይማኖተ ሰሚእ ጸንተን በሃይማኖተ ርእይ እናረጋግጣለን። ነገረ ሃይማኖትን ከአመክንዮ ባሻገር በእምነት የበለጠ እያወቅነው እንሄዳለን። ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በድጓው "ወአንተሰ ለእመ ትፈቅድ ታእምር ኅድግ ኅሊና ዘበምድር ወዕድዎሙ ለከዋክብት። እምዝንቱ ኵሉ ተልዒለከ በልቡናከ ሐሊ አሐደ ሥሉስ ዘኢይሴደቅ" ብሎ እንደተናገረው ከምድራዊ ሐሳብ ወጥተን ከከዋክብት በላይ ማሰብን (ሰማያዊ ሐሳብን) ይጠይቃል። ይህንን በደንብ እንመለከታለን።

## መንፈሳዊ ፍልስፍና

እውነትን መሠረት ያደረገ ፍልስፍና ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል እንጂ ከእግዚአብሔር አያርቅም። ከእግዚአብሔር የሚያርቅ ግልብ እና ጥልቅ ያልሆነ ፍልስፍና ነው። በነገራችን ላይ ፍልስፍና ማለት የጥበብ ፍቅር (Love of wisdom) ማለት ነው። እውነትን መሠረት ያደረገ ፍልስፍና መንፈሳዊ ፍልስፍና ነው። "ተፈልስፎ መንፈሳዊ" እንዲል (መጽሐፈ መነኮሳት)። አንዳንዶች ከእግዚአብሔር ለመለየት ልብ ወለዳቸውንና መሰለኛቸውን መሠረት አድርገው "ኢየሱስ ክርስቶስ የሚባል በዚህች ምድር አልነበረም" ብለው በድፍረት ይናገራሉ። እነዚህ አካላት ለሁሉ የተገለጠውን፣ ዓለም ሁሉ ስለእርሱ የሚናገረውን፣ ጥንታውያን መዛግብት ሁሉ ስለእርሱ የጻፉትን አይቀበሉም። ነገር ግን "አልነበረም" ለማለት መነሻችሁ ምንድን ነው ሲባሉ መልስ የላቸውም። እንዲህ ዓይነቶቹን "ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል" የሚለው ኃይለ ቃል ይገልጣቸዋል (መዝ.፲፫÷፩፤ መዝ.፶፪÷፩)።

አንዳንዶቹ ደግሞ በስሜት ሕዋሳቶቻችን አማካኝነት ካልተረዳነው የለም ማለት ነው ብለው ከልባቸው አፍልቀው ይናገራሉ። የስሜት ሕዋሳቶቻችን እኛ በማኅፀን እንደነበርን አያስታውሱም። ወይም ደግሞ ያለፈን ነገር አሁን ላይ አምጥተው ማሳየት አይችሉም። እንዲህ ስለሆነ ያለፈውን ዘመን መካድ ግን ትልቅ ስሕተት ነው። ትላንትን መካድ ዛሬን መካድ ነው። እኛ ሳንኖር እናቶቻችንና አባቶቻችን ነበሩ። እነርሱ በነበሩበት ዘመን የተከናወነን ድርጊት እኛ ስላልነበርን በየትኛውም የስሜት ሕዋሳታችን አማካኝነት መረዳት አንችልም። ያልነበርንበትን ዘመን ማወቅ የምንችለው በታሪክ ነው። እናቶቻችንና አባቶቻችን የነገሩንን መሠረት አድርገን እንናገራለን። እናቶቻችንና አባቶቻችን ያልነበሩበትን ዘመን ደግሞ ከእናቶቻቸውና ከአባቶቻቸው ጠይቀው ይረዳሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ እስከ አዳም ይደርሳል። አዳምም ቢሆን ከመፈጠሩ በፊት ስለነበረው ሁኔታ ማወቅ የሚችለው ከእርሱ በፊት የነበረውን አካል ጠይቆ ነው። የፈጠረው አካልም በራእይ እየተገለጠ ትእዛዝን ሰጥቶታል። በዚህ መንገድ እግዚአብሔር

ለእስራኤላውያን በግልጽ በዘፈቀደ ታይቷል። ይህንንም ሁሉም ለልጆቻቸው ነግረዋል። "ወኢኀብኡ እምደቂቆሙ ለካልእ ትውልድ" እንዲል (መዝ.፸፯÷፫)። ለማስረጃም ከሰማይ የወረደውን መና በመሶበ ወርቅ አድርገው አቆይተውታል።

በጠቅላላው ባለፈው ስላልነበርንበት ዘመን ማወቅ የምንችለው በታሪክ መሆኑን ነው። በዚህ ጊዜ መሰናክል የሚሆንብን ሐሰተኛ ታሪክ ነው። ታሪክ ሁሉ እውነት ላይሆን ይችላል። ሰው ውሸቱንም እውነት አድርጎ ጽፎ ለቀጣዩ ትውልድ ሊያስተላልፍ ይችላል። ብዙዎች የኢየሱስ ክርስቶስን በዚህች ምድር እየተመላለሰ ማስተማር ይቀበሉና ያደረጋቸውን ተአምራት ግን አይቀበሉም። ላለመቀበላቸው የሚያቀርቡት ምክንያት ግን ከተፈጥሮ ሕግ ያፈነገጠ ነገር እንዴት ሊያደረግ ይችላል? ብለው በማሰብ ነው። እነዚህ አካላት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አይቀበሉም። ነገር ግን በዘመኑ የነበሩ ሐዋርያት ያዩትን ጽፈዋል። አምላክ እንደመሆኑ የአምላክነት ሥራዎችን ሲሠራ ሁሉ አይቶታል። ይህ ከሆነ የተፈጥሮ ሕግን ለሰው ልጅ የሰጠ አምላክ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ ነገርን ቢያደርግ ይሳነዋልን!? ሐሰ አይሳነውም። የክርስቶስ ሰው መሆን ከ1 ዓ.ም እስከ 34 ዓ.ም ታይቶ የቀረና ለዚያ ትውልድ ብቻ የተገለጠ ለሌላው ግን በታሪክ የሚነገር ብቻ አድርጎ ማሰብ ትልቅ ስሕተት ነው። ሥጋው ደሙ ሁልጊዜም በቤተክርስቲያን እየተፈተተ፣ እርሱም በእርሱ ላመኑት ምእመናን ረድኤትን እየሰጠ ያለና የሚኖር ነው እንጂ። አሁንም ቢሆን ማንኛውም ሰው ከተጠራጠረ በሃይማኖት ሆኖ ልቡን ንጹሕ አድርጎ፣ ሱባኤ ገብቶ እግዚአብሔርን ማየት ይችላል። በክርስትና ሕይወት ትላንትንም ነገንም ዛሬ ላይ ሆኖ እንደዛሬ ማየት ይቻላል። "ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና" እንዲል (ማቴ.፭÷፰)።